# የአዳማ ከተማ አረንጓዴ መሰረተ ልማት ተሞክሮ ሰነድ



ህዳር 2012

# ማውጫ


1. መግቢያ ........ 1

 1.1. ዓላማ ........ 1

 1.2. የአረንጓዴ መሰረተ ልማት አስፈላጊነት ........ 1

2. የከተማ አረንጓዴ ልማት አፈፃፀም ........ 2

 2.1. የተፈጠረ የስራ ዕድል ........ 2

 2.2. የመሃል ከተማ አረንጓዴ ልማት ሽፋን ........ 3

 2.3. የከተማ አከባቢ ደን ሽፋን ........ 4

3. ተሞክሮ የሚወሰድባቸዉ የአረንጓዴ ልማት ዘርፎች ........ 5

 3.1. የመንገድ አካፋዮች ዳርቻዎች እና አደባበዮች ልማት ........ 5

 3.2. የሕዝብ መናፈሻ ፓርክ ልማት ........ 6

 3.3. የመኖሪያ ሰፈር አረንጓዴ ልማት ........ 8

 3.4. የተቋማት  ግቢ አረንጓዴ ልማት ........ 10

 3.5. የ ችግኝ ጣቢያ ልማት ........ 10

 3.6. የህዝብ ተሳትፎ በአረንጓዴ ልማት ........ 12

 3.7. የከተማ ደን ልማት ........ 13

4. የአረንጓዴ ቦታዎችን ማስከበር ........ 14

5. ያጋጠሙ ችግሮች ........ 14

6. ችግሮቹ የተፈቱበት አግባብ ........ 14

7. የተገኙ ዉጤቶች ........ 15

# 1. መግቢያ

የአዳማ ከተማ ከአዲስ አበባ  በስተ ደቡብ ምስራቅ በዘጠና ዘጠኝ ኪ.ሜ በድሮዉ መንገድ፣ በ84.7 ኪ.ሜ በአዲሱ ፈጣን መንገድ ርቀት ላይ የምትገኝ ስትሆን ከጅቡቲ ወደ አዲስ አበባ  እንዲሁም ወደ ምስራቅና ደቡብ ምሰራቅ የአገሪቱ ክፍሎች የሚያልፉ መንገዶች የሚያቂዋርጡዋት  ከፍተኛ የሆነ የንግድ የኮንፈረንስና የትራንስፖረት እንቅስቃሴ ያለባት የስምጥ ሸለቆዋ ዕንቁ በመባል የምትታወቅ ከተማ ነች፡፡የከተማዋ ሰፋት በፊት በነበረዉ የከተማ ማስተር ፕላን 13666 ሄክታር ሰሆን አዲስ የተሰራዉ ሰትራክቸራል ፕላን ከተማዋ ወደፊት 31185 ሄክታር  ስፋት እንደሚኖራት ያመለክታል፡፡ከተማዋ አየር  ንብረት ደረቅና ሞቃታማ  ሲሆን  የዝናብ ወቅቱም አጭር ነዉ፡፡

በቅርብ ዓመታት በዓለማችን እጅግ አሳሳቢ ከሆኑ ክስተቶች መካከል፡ የአለማችን የሙቀት መጠን መጨመር እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመጣዉ የአየር ንብረት ለዉጥ አንዱ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአለም አቀፍም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተለይ የከተማ የቆሻሻ አያያዝና የአረንጓዴ ልማት ትኩረት ከተሰጣቸዉ ሥራዎች ግንባር ቀደም ናቸዉ፡፡ የኢትዮጲያ መንግስትም የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ቀርፆ እየሠራ ይገኛል፡፡

የአዳማ ከተማ አስተዳደር የአረንጓዴ ልማት ፖሊሲን ከመተግበር አንፃር ከ 2005 ዓ.ም ጀምሮ በከተማ አረንጓዴ ልማት ዙሪያ በትኩረት በመስራት የአዳማ ከተማ በከተማዋ ያለዉን ከባድ የተፈጥሮ አየር ንብረት በመቋቋቀዋም አመቱን ሙሉ አረንጉዋዴ በመሆን  ለሌሎች የሀገራችን ከተሞች የተሞክሮ መቅሰምያ ማዕከል እየሆነች ትገኛለች፡፡ ባለፉት ሰባት(7) ዓመታት የተሰሩ ምርጥ ተሞክሮችም ከዚህ እንደሚከተለዉ ቀርቦዋል፡፡

## *1.1. ዓላማ*

አረንጓዴ ልማት ሥራዎች ላይ ቀጣይነት ያለዉ ተሳትፎን በመፍጠር የአረንጓዴ ልማት ሽፋንና ጥራት በማሻሻል የአከባቢ ብክለትን መቀነስ፤ ፅዱ፤አረንጓዴና ዉብ ለእንቨስትመንት እና ለኑሮ የተመቸች አዳማን መፍጠር እና የተገኘዉን ልምድ ወደ ሌሎች ከተሞች ማስፋት፡ ፡

## *1.2. የአረንጓዴ መሰረተ ልማት አስፈላጊነት*

በአሁኑ ጊዜ የአለማችን ዋነኛ አጀንዳ የሆነዉ የአለም ሙቀት መጨመርን አሱን ተከትሎ የመጣዉ የአየር ንብረት መዛባትን ለመቀነስና ብሎም ለመግታት በሚደረገዉ ርብርብ ዉስጥ


ሀገራችን ከፍተኛ እንስቃሴ በማድረግ ላይ እንደምትገኝ ይታወቃል። በመሆኑም የህንን ተግባራዊ ለማድረግ የአረንጉዋዴ ልማት ስትራቴጂ እና ስታንዳረድ በማዘገጀት በየደረጃዉ ለሚገኙ የከተማ አመራሮች ስልጠና በመስጠት ከተሞች የአረንጉዋዴ ልማት ስራን የእቅዳቸዉ አካል አድረገዉ እንዲተገብሩ የተለያዩ ድጋፎች ሲደረጉ ቆተዋል። ስለዚህ የከተሞች አረንጉዋዴ ልማት የመንግስት ስትራቴጂ ከመሆኑም ባሻገር በተለይ እንደ አዳማ ሞቃት የአየር ንብረት ያላቸዉ ከተሞች የነዋሪዎቻቸዉ ህልወና መሰረት መሆናቸዉ ታዉቆ ከተሞች ለአረንረጉዋዴ ልማት ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ነዉ።

# 2. የከተማ አረንጓዴ ልማት አፈፃፀም

በከተማችን የአረንጓዴ ልማት ስራ የመከናወነዉ በአነስተኛና ጥቃቅን በተደራጁ ማህበራትና የምግብ ዋስትና ፕሮገራም ተጠቃሚዎች ነዉ። በአጠቃላይ በማሕበራትና በልማታዊ ሴፍት ኔት ለ2087 ወንዶችና ለ2025 ሴቶች በአጠቃላይ ለ 4112 ሰዎች በአረንጓዴ ልማት ሥራ እድል እነድፈጠር ተደርጓል። በተጨማሪ ከደስትራል ማፕ በማዘጋጀት የአረንጓዴ ቦታዎችን በማስከበር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ለአረንጓዴ ልማት ሥራዎች  እንድ ዉሉ ተደርጓል። በአጠቃላይ ከ 2005 — 2011በ ዓ.ም ከላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች በመከናዎን የማሣል ከተማዋን አረንጓዴ ልማት ሽፋንን 161,099 ካ.ሜ ላይ ለማድረስ ተችሏል። በተጨማሪም 4,020.45 ሄክታር የአከባቢ ደን መልሶ የመልማት ሥራ እየተከናወነይገኛል።


## *2.1. የተፈጠረ የስራ ዕድል*

| የበጀት ዓመት | የተፈጠረ የሥራ እድል | | |
|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 2005 | 34 | 40 | 74 |
| 2006 | 97 | 42 | 139 |
| 2007 | 187 | 97 | 284 |
| 2008 | 273 | 175 | 448 |
| 2009 | 1335 | 1272 | 2607 |
| 2010 | 2087 | 2025 | 4112 |
| 2011 | 3477 | 3416 | 6893 |




## *2.2. የመሃል ከተማ አረንጓዴ ልማት ሽፋን*

| የበጀት ዓመት | የለማ የመሬት ስፋት /ካ.ሜ/ |
|---|---|
| 2005 | 7132 |
| 2006 | 14811 |
| 2007 | 47912 |
| 2008 | 60968 |
| 2009 | 65426 |
| 2010 | 161099 |
| 2011 | 219044 |




## *2.3. የከተማ አከባቢ ደን ሽፋን*

| **የደን ሥፍራ ስም** | **በማስተር ፕላን ላይ የተቀመጠ (ሄክታር)** | **የለማ ቦታ ስፋት (ሄክታር)** | **አፈፃፀም/%/** |
|---|---|---|---|
| ቦኩ | 1,531.38 | 1,506.90 | 98.40 |
| ድብብሳ | 487.47 | 479.01 | 98.26 |
| ምግራ እና ዳቤ | 536.29 | 492.95 | 91.92 |
| ቀጨማ | 365.26 | 358.37 | 98.11 |
| አሮጌ አዳማ | 76.76 | 75.10 | 97.84 |
| ስሬ አባቡኔ | 1,068.41 | 1,066.15 | 99.79 |
| ኩርፋ ጉቱ እና ሶሌ | 58.49 | 41.97 | 71.76 |
| | **4,124.06** | **4,020.45** | **97.49** |

# 3. ተሞክሮ የሚወሰድባቸዉ የአረንጓዴ ልማት ዘርፎች

## *3.1. የመንገድ አካፋዮች ዳርቻዎች እና አደባበዮች ልማት*

በከተማዋ የሚገኙ ዋና ዋና እና ዉስጥ ለዉስጥ መንገዶች 71,578.44 ካሜ የመንገድ አከፋዮችና ዳርቻዎች ልማት የተከናወነ ሲሆን ይህም በከተማዋ ከመኪኖች የሚወጣዉን ጭስና ሙቀት በመምጠጥ እና ነዋሪዎች ከትራፊክ አደጋ እንዲጠበቁ በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እየሰጠ ይገኛል::





## 3.2. የሕዝብ መናፈሻ ፓርክ ልማት

አቦ ፓረክከ CRGE በተገኘ አነስተኛ በጀት 70,000 ካ.ሜ. ቦታ ላይ የሕዝብ መናፈሻ ፓርክ በማቋቋምና ከከተማ አስተዳደሩ 10 ሚሊዮን ብር በጀት በማስመደብ የተለያዩ የፓረክ ኮመፖነነቶችን ማለትም ካፍቴሪያ፣ የተለያዩ የቤት ዉስጥ ጫወታዎች የሚያገለግሉ ክፍሎች፣ ኢንተርኔት ካፌ የተለያዩ የስፖርት ሜዳዎች እንዲሁም የሙሽራ መናፈሻ በማስገነባት አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ የአካባቢዉ ወጣቶች አልባሌ ቦታ እንዳይዉሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከተ ሲሆን በተጨማሪም ሚጊራ የደን ፓርክ በ90 ሄክታር መሬት ላይ ተመስረቶ ዙሪያዉን አጥር በማጠር እና የተለያዩ ፋሲሊቲዎችን በማሙዋላት ለአገልግሎት እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

## የኦቦ ፓርክ ከፊል ገጽታዎች




## የስፖርት ሜዳዎች




የሚጊራ ፓርክ



## *3.3. የመኖሪያ ሰፈር አረንጓዴ ልማት*

**በፕላን የተለዩ አረንጉዋዴ ስፍራ ያላቸዉ መኖሪያ ሰፈሮች ነዋሪዎቻቸዉነ በማስተባበር እና የተለያዩ ተቋዋማትን በማስተባበር** 10 የአረንጓዴ ቦታዎች(17,400 ካ.ሜ) በማልማት ሕዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሎዋል







## *3.4. የተቋማት ግቢ አረንጓዴ ልማት*

5564 ካ.ሜ የመንግስት ተቋማት ግቢ ዉስጥ አረንጓዴ በማድረግ እንደተሞክሮ በመጠቀም ለማስፋት ጥረት እተደረገ ይገኛል፡፡

እንዲሁም በአባ ገዳ የስብሰባ ማእከልና በአዳማ ዩኒቨርስቲ ጊቢ ዉስጥ ከ30 ሄክታር በላይ ላንድ ሰኬፑን ጠብቆ የለማ አረንጓዴ ስፍራ ይገኛል







## *3.5. የችግኝ ጣቢያ ልማት*

በአንድ ጊዜ  ሁለት ሚልዮን ችግኝ  ሊፈላበት የምችል በ 20,000 ካ.ሜ ቦታ ላይ በመቋቋም በየዓመቱ  ደረጃቸዉን የተጠበቁ አገር በቀልና የዉጭ ዝሪያ ችግኞችን በማፍላት መትከልና

ለከተማዋ ነዋሪዎችና ለአካባቢዉ አርሶ አደሮች በነፃ በማሰራጨት ከፍተኛ ጠቀሜታ እየሰጠ ሲሆን፤

በተጨማሪም የቆሻሻ መጣያ የነበሩትን ቦታዎች በማፅዳት ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በማስተላለፍ ችግኝ አፍልቶ በመሸጥና አካባቢዉን በማስዋብ ገቢ ማስገኛ ማድረግ፤ሰፊ ስራ ተሰርቶዋል

የማዘጋጃ ቤቱ ችግኝ ጣቢያ





የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋዋማት ችግኝ ማፍያ



## 3.6. የህዝብ ተሳትፎ በአረንጓዴ ልማት

**የከተማችንን ነዋሪዎች በአፈርና ዉሃ ጥበቃ ስራዎች በችግኝ ጉድጉዋድ ዝግጅትና በችግኝ ተከላ ፕሮግራም በስፋት በማሳተፍ አመርቂ ዉጤት ተመዝግቦዋል**

## 3.7. የከተማ ደን ልማት

**መናማ ኮምፖስት ፕሮጀክት ዕገዛ ከአዳማ ዩኒቨርሰቲ ጋር በመተባበር በከተማዉ ዙሪያ የሚገኙ የደን መሬቶችንበጥናት በመለየትና የተለዩ ቦታዎችን በህብረተሰብ ተሳትፎ፣ በአርሶአደር ማህበራት፤ በምግብ ዋስትና ተጠቃሚዎች የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ስራዎችን በመስራት፤ ክረምት በችግን ተከላ ፕሮገራሞች በስፋት በመሳተፍ የተጎዱና የተራቆቱ ቦታዎች ተመልሰዉ እንዲያገግሙ ሆኖዋል።**







**የ**

# 4. የአረንጓዴ ቦታዎችን ማስከበር

**የአረንጉዋዴ ቦታዎችን ከወራራ ለመከላከል ይቻል ዘንድ የከተማዋን አረንጉዋዴ ስፍራ በካዳስተራል ፐላን ከተሰራ በሁዋላ 33,500.1 ሄከታር ቦታ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካረታ ተሰርቶላቸዋል**







# 5. ያጋጠሙ ችግሮች

የአረንጉዋዴ ልማት እሳቤ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዘርፉ በርካታ ተግዳሮቶች አጋጠመዉታል፡፡ ከነዚህም ዉስጥ

- በተለያየ ጊዜ የሚቀያየሩ አመራሮች ለስራዉ እኩል ትኩረት ያለመስጠት
- ስራዉን ለመምራትም ሆነ ለመፈፀም ተገቢ የሆነ ባለሙያ ያለመመደብ
- የዉሃ እጥረት
- በከተማዉ ዉሰጥ የቤት እንስሳት በተለይም የጋሪ ፈረሶችና ግመሎች በብዛት መለቀቅ
- የአረንጉዋዴ ቦታዎቸን ለሌላ ተግባር የማዋል ችግር

# 6. ችግሮቹ የተፈቱበት አግባብ

- በየጊዜዉ ለሚቀያየሩ የክፍለ ከተማና የቀበሌ አመራሮች ስልጠና መስጠት
- ከዘርፉ ጋር ተያያዥ የሆኑ በለሙየዎችን መመደብና በቅጥር ማሙዋላት
- የዉሃ መስመሮችን መዘረጋት እንዲሁም ሶስት ቦቴዎችን በግዥ ሰባት ቦቴዎችን በኪራይ በማቅረብ በቦቴ ዉሃ በማጠጣት

- በከተማ ዉስጥ የሚለቀቁ እንስሳትን ማቆያ በማዘጋጀት ና በመቅጣት ያረጁና የተጣሉ ፈረሶችን ስፓና ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር ማስወገድ እንዲሁም ለደን ቦታዎች ጥበቃዎችን በመቅጠርና ለመንከባከብ ፍቃደኛ ለሆኑ ባለ ሀብቶችና ድረጅቶች በዉል በማስተላለፍ እንዲጠበቁ በማድረግ

በአጠቃላይ ዘርፉ ከፍተኛ ማነቆዎች ያሉበት ከፍተኛ መሰዋዕተነትን ፡ በጀትን እንዲሁም በየደረጃዉ የሉ አመራሮችን ቁረጠኝነት የመጠይቅ ሲሆን ሁሉን ነገሮች ተቁዋቁሞ ከተሰራበት ግን ለሀገርም ሆነ ለህዝብ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለዉ፡፡

# 7. የተገኙ ዉጤቶች

- የአረንጉዋዴ ልማት ስራ ቀጣይነት ባለዉ መልኩ እንዲከናወን የአሰራር ሰርዓት መዘረጋቱ
- የከተማዋ አረንጉዋዴ ሽፋን ከአመት ወደ አመት መጨመሩ
- የተጎዱና የቆሸሻ መከመሪያ የሆኑ ቦታዎች ለምተዉ ጤናማ መሆናቸዉ በከተማዉ የነበረዉ የአቡዋራና ሙቀት መጠን መቀነስ እንዲሁም የዝናብ ሽፋን መጨመር
- በተሰራዉ የአፈርና የዉሃ ጥበቃ ስራ ከተማዋን የሚያጠቃት የጎርፍ መጠን መቀነስ
- ነዋሪዎች ጥላ የላቸዉን ነፋሻማ ማረፊያ ቦታዎችን በአካባቢያቸዉ ማግኘታቸዉ
- ስራዉ ትኩረት ማግኘቱና አብዛኛዉ ህብረተሰብ ክፍል በየመኖሪ ቤቱ ዛፍ መትከልን ባህል ማድረጉ
- ዘርፉ ከፍተኛ የሆነ የስራ ዕድል ማስገኘቱ
- ከተለያዩ ባለድረሻ አከላት ጋር በትብር የመስራት ባህል መዳበሩ ዋነኞቹ ናቸዉ